District of Columbia
Office of the State Superintendent of Education

የኮሎምቢያ ዲስትሪክት
የእስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ጽ/ቤት

# የተማሪ ትራንስፖርት
# የወላጅ እና የቤተሰብ መመሪያ

**ማውጫ**


ኦ/ኤስ/ኤስ/ኢ ዲ/ኦ/ቲ፥ ብቁ የሆኑ የአካል ጉዳት ያለባቸውን ተማሪዎች ማጓጓዝ 1

ለተማሪ ማጓጓዣ ብቁ የሚሆነው ማን ነው? ለልጄ አገልግሎቱን እንዴት ማግኘት እችላለሁ? 1

የትምህርት ቤት አውቶቡስ የጉዞ መርሃግብር 2

የትምህርት ቤት አውቶቡስ መስመር ማዘጋጀት 2
የመስመር መርሃግብር ለውጦች 2
የጉዞ መስመሮች 2
በአውቶቡስ ላይ የጉዞ ጊዜ 3

ልጆችን የመቀበል እና የማውረድ መመሪያዎች 3

ጠዋት ተማሪዎችን የመውሰድ ደንቦች 3
በሰዓቱ ትምህርት ቤት መድረስ 3
ከሰዓት በኋላ ተማሪዎችን እቤታቸው የማውረድ ደንቦች 4
እራሳቸውን የቻሉ ተማሪዎችን ማውረድ (ISD-አይ/ኤስ/ዲ) 4

የወላጅ እና የአሳዳጊ ሚናዎች እና ሃላፊነቶች 4

የመገኛ አድራሻን መረጃ ወቅታዊ ማድረግ 4

የአውቶቡስ ሹፌር እና የረዳቱ ሃላፊነቶች እና ግዴታዎች 5

የአውቶቡስ ሹፌር እና የረዳቱ ስልጠና 5
በአውቶቡስ ላይ የተማሪ ባህሪያት 5
በትምህርት ቤት አውቶብሶች ላይ ከተማሪ የሚጠበቁ ባህሪያት 6
የወላጅ የመረጃ ማእከል ምንድን ነው? 6

አቤቱታ/ቅሬታን ማስመዝገብ 6

አቤቱታ/ቅሬታ ካቀረቡ በኋላ የሚከተለው ምንድን ነው? 7

ተደጋግመው የሚነሱ ጥያቄዎች 7

ተጨማሪ የመረጃ እና የመገኛ ዝርዝሮች 9

## ኦ/ኤስ/ኤስ/ኢ ዲ/ኦ/ቲ፥ ብቁ የሆኑ የአካል ጉዳት ያለባቸውን ተማሪዎች ማጓጓዝ

የእስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ የተማሪዎች መጓጓዣ ክፍል (OSSE DOT-ኦ/ኤስ/ኤስ/ኢ ዲ/ኦ/ቲ) የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ነዋሪ ለሆኑ እና ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች አዎንታዊ በሆነ መንገድ የትምህርት እድሎችን የሚደግፍ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ አስተማማኝ እና የተቀላጠፈ የትራንስፖርት/የመጓጓዣ አገልግሎት ይሰጣል። ለመጓጓዣ አገልግሎቶች ብቁነት የሚወሰነው በተማሪው የግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP-አይ/ኢ/ፒ) ሲሆን ይህም ተማሪው በተመዘገበበት የአካባቢያዊ የትምህርት ወኪል (LEA-ኤል/ኢ/ኤ) የተዘጋጀ ነው። የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA-አይ/ዲ/ኢ/ኤ) የአካል ጉዳት ላለባቸው ተማሪዎች በሙሉ ነጻ፣ ተስማሚ የህዝብ የትምህርት አገልግሎት (FAPE-ኤፍ/ኤ/ፒ/ኢ) የመስጠት አስፈላጊነትን ያጠቃልላል። አይ/ዲ/ኢ/ኤ *መጓጓዣ* የሚለውን አንድ የአካል ጉዳት ያለበት ልጅ ከልዩ ትምህርት ተጠቃሚ እንዲሆን ለማገዝ እና ኤፍ/ኤ/ፒ/ኢ ማግኘት እንዲችል የሚያግዝ አስፈላጊ የሆነ ተያያዥ አገልግሎት[1] እንደሆነ ይገልጸዋል። ብቁ የሆኑ ተማሪዎች እድሜያቸው ከ3 እስከ 22 ባለው የእድሜ ክልል ውስጥ ይገኛሉ። የትምህርት ቤት አውቶቡስ፣ የዲሲ ዋን ካርድ ኤንድ ፓሬንት ሪምበርስመንት የሚሉትን ጨምሮ የተለያዩ አይነት የመጓጓዣ አማራጭ መንገዶች አሉ።

## ለተማሪ ማጓጓዣ ብቁ የሚሆነው ማን ነው? ለልጄ አገልግሎቱን እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

የአካል ጉዳት ላለበት አንድ ተማሪ የልዩ ትምህርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች ማግኘት መቻልን ለማገዝ የመጓጓዣ አገልግሎት ማግኘት ያስፈልገዋል ወይስ አያስፈልገውም የሚለውን ለእያንዳንዱ ተማሪ በተናጠል መወሰን እንዲሁም አገልግሎቱ የሚያስፈልገው ከሆነም የመጓጓዣ አገልግሎቱ እንዴት መተግበር አለበት የሚለውን መወሰን ልጅዎት በሚገኝበት ኤል/ኢ/ኤ ውስጥ የሚገኘው የአይ/ኢ/ፒ ቡድን ሃላፊነት ነው። የተማሪዎችን ለመጓጓዣ ብቁነት በተመለከተ ማንኛውም አይነት ጥያቄዎች በልጅዎት ትምህርት ቤት ውስጥ ለሚገኙ የቢሮ ሰራተኞች መቅረብ አለባቸው።

በአይ/ኢ/ፒ ቡድኑ ተማሪው ለመጓጓዣ አገልግሎቶች ብቁ ሆኖ ከተገኘ፣ ኤል/ኢ/ኤው የመጓጓዣ መጠየቂያ ቅጽ (TRF-ቲ/አር/ኤፍ) ለኦ/ኤስ/ኤስ/ኢ ዲ/ኦ/ቲ ማስገባት አለበት። ይህ ቲ/አር/ኤፍ እንደደረሰው ኦ/ኤስ/ኤስ/ኢ ዲ/ኦ/ቲ ወዲያውኑ ጥያቄውን ማስተናገድ ይጀምራል። ለመጓጓዣ አገልግሎቶች ብቁ የሆኑ ተማሪዎች ጥያቄው ከኤል/ኢ/ኤ በቀረበ በአስር ቀናት ውስጥ ይመደባሉ።

ማንኛውም በዲ/ኦ/ቲ መኪና የማይጓጓዝ ተማሪ ለ 'ኪድስ ራይድ ፍሪ' ብቁ ነው። የፐብሊክ ወይም የፐብሊክ ቻርተር ትምህርት ቤት የሚከታተል ተማሪ ከትምህርት ቤቱ የመታወቂያ አስተዳደር የዲሲ ዋን ካርድ መጠየቅ ይችላል። ተማሪው ፐብሊክ ያልሆነ ትምህርት ቤት ወይም ፕሮግራም የሚከታተል ከሆነ፣ የአይ/ኢ/ፒ ቡድኑ አንድ አባል ኦ/ኤስ/ኤስ/ኢ ዲ/ኦ/ቲን በማናገር የዲሲ ዋን ካርድ መጠየቅ ይኖርበታል። በተጨማሪም፣ የተማሪው መኖሪያ ወይም ትምህርት ቤት/ፕሮግራም ከዲስትሪክቱ ውጭ የሚገኝ ከሆነ፣ የሜትሮ ማጓጓዣ ክፍያ እገዛ ለመጠየቅ የተማሪው ትምህርት ቤት የአይ/ኢ/ፒ ቡድኑ አንድ አባል ኦ/ኤስ/ኤስ/ኢ ዲ/ኦ/ቲን ማናገር ይኖርበታል።

ለወላጅ ማካካሻ/ተመላሽ ክፍያ ብቁ የሆኑ ተማሪዎች የተመላሽ ገንዘብ ማመልከቻ ለማስገባት ወደ የወላጅ መረጃ ማእከል (PRC-ፒ/አር/ሲ) በስልክ ቁጥር 202 576-5000 መደወል አለባቸው።

---

[1] 34 C.F.R. §300.34(a)

# የትምህርት ቤት አውቶቡስ የጉዞ መርሃግብር

## የትምህርት ቤት አውቶቡስ መስመር ማዘጋጀት

የትምህርት ቤት አውቶቡስ መስመሮች ስልታዊ በሆነ መንገድ የሚዘጋጁ ናቸው። ኦ/ኤስ/ኤስ/ኢ ዲ/ኦ/ቲ የትምህርት ቤት አውቶቡስ መስመሮችን ሲያዘጋጅ የተለያዩ መሳሪያዎችን ማለትም፣ የመስመር ምደባ ሶፍትዌር፣ የጂ/ፒ/ኤስ ዳታ እና የሾፌሮችን ግብረ መልስ በመጠቀም ነው። የትምህርት ቤት የአውቶቡስ መስመሮችን ለማዘጋጀት ታሳቢ የሚደረጉ በርካታ ነጥቦች አሉ፥

- ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት ቦታ
- የተማሪው አድራሻ
- ትምህርት የሚጀምርበት ሰዓት
- በአውቶቡስ ውስጥ ያሉት የተማሪዎች ብዛት
- ለተወሰኑ ቦታዎች የትራፊክ ፍሰት ሁኔታ

## የመስመር መርሃግብር ለውጦች


በተለያዩ ምክንያቶች የመስመር ለውጦች አመቱን ሙሉ ሊከሰቱ ይችላሉ። እነዚህም የሚከተሉትን ሊያጠቃልሉ ይችላሉ፥

- የቅበላ ለውጦች
- በተማሪዎች ምደባ ላይ የሚኖሩ ለውጦች
- የአድራሻ ለውጦች

በተጨማሪም ኦ/ኤስ/ኤስ/ኢ ዲ/ኦ/ቲ የተሻለ የጉዞ ሰዓት፣ በጣም ጥሩ የሆነ ተማሪዎችን የመረከቢያ ሰዓቶች እንዲኖር ለማድረግ ወይም ትምህርት ቤት ውስጥ የጠዋት ደውል ከመደወሉ በፊት በሰዓቱ መድረስን ለማሻሻል የጉዞ መስመሮችን ሊቀይር ይችላል። ወላጆች ማንኛውንም የጉዞ መስመር እና የሰዓት ለውጦች አስመልክቶ ከወላጆች የመረጃ ማእከል ስልክ ይደወልላቸዋል።

## የጉዞ መስመሮች

ኦ/ኤስ/ኤስ/ኢ ዲ/ኦ/ቲ ማንኛውንም ለውጥ በሶስት የስራ ቀናት ውስጥ ለማጠናቀቅ ጠንክሮ ይሰራል። ነገር ግን፣ የአውቶቡስ የጉዞ መስመር ለውጦች የለዉጡ ጥያቄ ከቀረበበት እለት አንስቶ እስከ 10 የስራ ቀናት ሊፈጁ ይችላሉ።



### በአውቶቡስ ላይ የጉዞ ጊዜ

“የጉዞ ጊዜ” የሚባለው ተማሪው ከቤት ወይም ከሌላ ከተመደበ ቦታ ከተሳፈረበት አንስቶ ትምህርት ቤት ውስጥ ወይም ሌላ ተያያዥ አገልግሎት ቦታ እስኪደርስ ያለው ጊዜ ወይም፣ ተማሪው ከትምህርት ቤት ወይም ሌላ ተያያዥ አገልግሎት ቦታ ከተሳፈረበት ግዜ አንስቶ ከቤት ወይም ከሌላ ከተመደበ ቦታ እስኪደርስ ያለው ጊዜ ነው። የመንገድ መዘጋጋት፣ የአየር ሁኔታ፣ እና አንዳንድ ያልተገመቱ ሁኔታዎች የጉዞ ጊዜው ላይ ለውጥ ሊያመጡ ይችላሉ።

በአሁኑ ሰዓት በኦ/ኤስ/ኤስ/ኢ ዲ/ኦ/ቲ የወጡ መደበኛ የጉዞ ሰዓታት እንደሚከተሉት ናቸው፥

- 75 ደቂቃ፣ የሚከታተሉት ፕሮግራም በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ የሚገኝ ከሆነ፤
- 75 ደቂቃ፣ የሚከታተሉት ፕሮግራም ከኮሎምቢያ ዲስትሪክት ስድስት ማይል ወይም ከዛ በታች እርቀት ላይ የሚገኝ በሜሪላንድ ወይም ቨርጂኒያ ውስጥ የሚገኝ ከሆነ፤
- 90 ደቂቃ፣ የሚከታተሉት ፕሮግራም ከኮሎምቢያ ዲስትሪክት ከስድስት ማይል በላይ እና ከ 15 ማይል በታች እርቀት ላይ የሚገኝ በሜሪላንድ ወይም ቨርጂኒያ ውስጥ የሚገኝ ከሆነ፤
- 120 ደቂቃ፣ የሚከታተሉት ፕሮግራም ከኮሎምቢያ ዲስትሪክት ከ 15 ማይል በላይ እርቀት ላይ የሚገኝ በሜሪላንድ ውስጥ የሚገኝ ከሆነ፤

## ልጆችን የመቀበል እና የማውረድ መመሪያዎች

በኦ/ኤስ/ኤስ/ኢ ለዲ/ኦ/ቲ ህጎች እና የአሰራር መመሪያዎች አስፈላጊ በሆኑ የአካባቢያዊ እና የፌደራል ህጎች መሰረት ደህንነቱ የተጠበቀ፣ አስተማማኝ እና ሰዓትን የሚያከብር የተማሪዎች የመጓጓዣ አገልግሎት የአካል ጉዳት ላለባቸው ተማሪዎች ለመስጠት በትጋት ይሰራል። እነዚህ ደረጃዎች ኦ/ኤስ/ኤስ/ኢ ሰራተኞች፣ የዲሲ ኤጀንሲ ሰራተኞች እና የኮንትራት ሰራተኞችን ጨምሮ ለሁሉም የአካል ጉዳት ላለባቸው የዲሲ ተማሪዎች የልዩ ትምህርት የመጓጓዣ አገልግሎት ሰጭዎች በሙሉ ተፈጻሚ የሚሆኑ ናቸው።

### ጠዋት ተማሪዎችን የመውሰድ ደንቦች

- ጠዋት ላይ የተማሪዎች ማጓጓዣ በቦታው የሚደርስበት ጊዜ የ30 ደቂቃ ክፍተት አለው፤ ይህም ከታቀደው ተማሪውን የመጫኛ ሰዓት 15 ደቂቃ ቀድሞ እና ከታቀደው የተማሪ መጫኛ ሰዓት በ15 ደቂቃ ዘግይቶ ነው።
- በዚህ የጊዜ ክፍተት ውስጥ ልጅዎት ዝግጁ ሆኖ አውቶብሱን እየጠበቀ መሆን አለበት ወይም ደግሞ አውቶብሱ በቦታው ሲደርስ በሩ ጋር ሆኖ ማየት መቻሉ በጣም አስፈላጊ ነው። የአውቶቡስ እረዳቱ ወደ ውጭ በሩ በመቅረብ መራመድ ለሚችሉ ተማሪዎች ለሶስት ደቂቃ ያህል መራመድ ለማይችሉ ተማሪዎች (ዊልቼር ተጠቃሚዎች) ደግሞ ለአምስት ደቂቃ ያህል ይጠብቃል። እባክዎትን የአውቶቡስ እረዳቱ የመኖሪያ ቅጽርዎትን በር የማንኳኳት ሃላፊነት የሌለበት መሆኑን ልብ ይበሉ። (በቤት ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ፣ ይህ ብዙ ጊዜ የቤቱ በር ነው የሚሆነው፤ እንግዳ መቀበያ (ሎቢ) ባለው አፓርታማ ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ ደግሞ ይህ የህንጻው ዋና መግቢያ በር ነው የሚሆነው - የአውቶቡስ እረዳቶች የአፓርታማ ህንጻዎች ውስጥ እንዲገቡ አይፈቀድላቸውም።) ውሾች እና የተቆለፉ በሮች የአውቶቡስ እረዳቱ ወደ ውጭኛው በር እንዳይቀርብ ሊያግዱ ይችላሉ።
- አውቶብሱ ከተገለጸው ሰዓት ቀድሞ ወይም ዘግይቶ የሚደርስ ከሆነ ወላጆች በፒ/አር/ሲ ስምሪት ቡድን አባል አማካኝነት በስልክ ተደውሎ የሚነገራቸው ይሆናል።

### በሰዓቱ ትምህርት ቤት መድረስ

በሰዓቱ ትምህርት ቤት መድረስ በኦ/ኤስ/ኤስ/ኢ ዲ/ኦ/ቲ በዋናነት ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ነገሮች አንዱ ነው። የኦ/ኤስ/ኤስ/ኢ ዲ/ኦ/ቲ ግብ ተማሪዎች በ20 ደቂቃ ክፍተት ውስጥ ትምህርት ቤት እንዲደርሱ ነው፤ ደውል ከመደወሉ በፊት ከ30 ደቂቃ በላይ ሳይቀድሙ እና ደውል ከመደወሉ በፊት ከ10 ደቂቃ በኋላ ሳይዘገዩ። ለምሳሌ፣ ደውል መደወያ ሰዓቱ 8:00 a.m. ከሆነ፣ በሰዓቱ የሚደርስ አውቶቡስ ከ7:30 a.m. እስከ 7:50 a.m. ባለው ጊዜ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ይደርሳል ማለት ነው።

## ከሰዓት በኋላ ተማሪዎችን እቤታቸው የማውረድ ደንቦች

- ከሰዓት በኋላ አውቶብሱ ከታቀደው ተማሪዎችን እቤታቸው የማድረሻ ሰዓት የሚዘገይ ከሆነ ወላጆች፣ አሳዳጊዎች እና የትምህርት ቤት ባለስልጣናት በፒ/አር/ሲ ስምሪት ቡድን አባል አማካኝነት በስልክ ተደውሎ የሚነገራቸው ይሆናል።
- ከሰዓት በኋላ የተማሪዎች ማጓጓዣ በቦታው የሚደርስበት ጊዜ የ30 ደቂቃ ክፍተት አለው፤ ይህም ከታቀደው ተማሪውን የማውረጃ ሰዓት 15 ደቂቃ ቀድሞ እና ከታቀደው የተማሪ የማውረጃ ሰዓት በ15 ደቂቃ ዘግይቶ ነው።
- በከሰዓት በኋላ የማውረጃ አድራሻው ላይ ተማሪውን የሚቀበል እድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ ስልጣኑ የተሰጠው ሰው ሊኖር ይገባል። እባክዎትን በተማሪው የመጓጓዣ መገለጫ ላይ የተማሪው መገኛ አድራሻ በሚለው ክፍል ውስጥ የዚህ ሰው ስም መጠቀስ ያለበት መሆኑን ልብ ይበሉ።

## እራሳቸውን የቻሉ ተማሪዎችን ማውረድ (ISD-አይ/ኤስ/ዲ)

ወላጆች እና አሳዳጊዎች እራሳቸውን የቻሉ ተማሪዎችን ማውረድ በተፈቀደው የከሰዓት በኋላ ማውረጃ ቦታ አዋቂ በሌለበት ሁኔታ እንዲወርዱ መፍቀድ ይችላሉ። ኦ/ኤስ/ኤስ/ኢ ዲ/ኦ/ቲ የአይ/ኤስ/ዲ ሙብቶችን ለመቀበል፣ የልጅዎት እድሜ ቢያንስ 12 ዓመት የሆነው መሆን ያለበት ሲሆን በአይ/ኢ/ፒያቸው ላይ የልዩ ፕሮግራም ተጠቃሚ (ASP-ኤ/ኤስ/ፒ) ምድብ ስር የተገለጹ መሆን አለባቸው። የአይ/ኤስ/ዲ ማመልከቻ ቅጾች በተማሪው ኤል/ኢ/ኤ በኩል ማግኘት ይቻላል። የአይ/ኤስ/ዲ ቅጹ በኤል/ኢ/ኤው በኩል ተማሪዎቹ በሚማሩበት ትምህርት ቤት ስልጣኑ ባለው ተጠሪ አማካኝነት በተማሪው የመጓጓዣ ፕሮፋይል ላይ አፕሎድ መደረግ አለበት። አይ/ኤስ/ዲ ተማሪዎች መኖሪያቸውን ከፍተው መግባት መቻል እንዳለባቸው ልብ ይበሉ (ማለትም ቁልፍ ወይም ሌሎች ተቀባይነት ያላቸው ከፍቶ የመግቢያ መንገዶች)።

# የወላጅ እና የአሳዳጊ ሚናዎች እና ሃላፊነቶች

ሁለትዮሽ የሆነ፣ ውጤታማ መስተጋብር ከአውቶቡስ ሹፌሩ እና የአውቶቡስ ሰራተኛው ጋር መልካም የሆነ የስራ ግንኙነት ለመፍጠር በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። በተጨማሪም ሹፌሩ እና እረዳቱ የልጅዎትን ልዩ ባህሪያት እና ፍላጎቶች ለመረዳት ጥሩ መንገድ ነው። እባክዎትን እራስዎትን ከሹፌሩ እና ከእረዳቱ ጋር ያስተዋውቋቸው፣ ምንም አይነት ጥያቄ ካለዎትም እነሱን ከመጠየቅ ወደኋላ አይበሉ። ነገር ግን፣ የትምህርት ቤት አውቶብሱ በርካታ ተማሪዎችን እንደሚጭን እና በመስመሩ ላይ ያለ እያንዳንዱን ተማሪ ከመነሻ ቦታው ለመጫን እና ትምህርት ቤት በሰዓቱ ለመድረስ በእያንዳንዱ ማቆሚያ ቦታ ሊቆይ የሚችለው ጥቂት ደቂቃዎችን ብቻ እንደሆነ ልብ ይበሉ። ወላጆች ከሹፌሮች እና ከረዳቶቻቸው ጋር የሚኖራቸው የጋራ መከባበር ያለበት መልካም ግንኙነት በአውቶብሱ ውስጥ በጣም ጥሩ የሆነ መንፈስ እንዲኖር ያደርጋል።

በተጨማሪም፣ ወላጆች ልጆቻቸው በየእለቱ ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ እና በሰዓቱ ትምህርት ቤት ድረስ መጓጓዛቸውን እና መድረሳቸውን የማረጋገጥ ሃላፊነት እና ግዴታ አለባቸው። ወላጆች እና አሳዳጊዎች የሚከተሉትን ማድረጋቸው በጣም አስፈላጊ ነው፥

- ከአውቶቡስ ሹፌሩ እና ከረዳቱ ጋር ግልጽ በሆነ መልኩ መግባባት መቻል
- የመገኛ አድራሻን በትክክል እና ወቅታዊ አድርጎ መዝግቦ ማስቀመጥ
- ተማሪዎች ጠዋት ወደትምህርት ቤት የሚሄደው አውቶቡስ ላይ ለመሳፈር ዝግጁ መሆናቸውን ማረጋገጥ
- ከሰዓት ከትምህርት ቤት ሲመለሱ የሚቀበላቸው አዋቂ ሰው መኖሩን ማረጋገጥ

## የመገኛ አድራሻን መረጃ ወቅታዊ ማድረግ

ኦ/ኤስ/ኤስ/ኢ ዲ/ኦ/ቲ ስልክ ቁጥሮች፣ የአደጋ ጊዜ ተጠሪ ቁጥሮች፣ እና የኢሜይል አድራሻዎችን ያካተተ ወቅታዊ የሆነ የመገኛ አድራሻ እንዲኖረው ያስፈልጋል። **እባክዎትን የልጅዎት ትምህርት ቤት ወቅታዊ የሆነ የመገኛ አድራሻ መረጃ ያለው መሆኑን ያረጋግጡ፤ ይህም ኦ/ኤስ/ኤስ/ኢ ዲ/ኦ/ቲ የአውቶቡስ ሁኔታን፣ የመስመር ለውጥ፣ እና የአደጋ ጊዜ መረጃዎችን በተመለከተ መረጃ ይሰጥዎት ዘንድ ያስችለዋል።** ኦ/ኤስ/ኤስ/ኢ ዲ/ኦ/ቲ በመጓጓዣ ሲስተም ውስጥ ያለን የመገኛ አድራሻ ወቅታዊ ማድረግ ወይም መቀየር አይችልም።

# የአውቶቡስ ሹፌር እና የረዳቱ ሃላፊነቶች እና ግዴታዎች

## የአውቶቡስ ሹፌር እና የረዳቱ ስልጠና

ብቃት ያለው እና ስልጠና የወሰደ ሰራተኛ በመቅጠር የማጓጓዣ አገልግሎት ለተማሪዎች እንዲሰጥ በማድረግ፣ ኦ/ኤስ/ኤስ/ኢ ዲ/ኦ/ቲ አገልግሎት ለምንሰጣቸው ተማሪዎች የላቀ አገልግሎት ለመስጠት ይጥራል። እያንዳንዱ ሹፌር የኮሜርሺያል የመንጃ ፈቃድ (CDL- ሲ/ዲ/ኤል) እና የትምህርት ቤት አውቶቡስ ለመንዳት ተስማሚ የሆኑ ድጋፎች ያሉት ነው። እያንዳንዱ የአውቶቡስ ሹፌር በእያንዳንዱ ተማሪዎችን ለማጓጓዝ በታዘዘ አውቶቡስ ላይ ስልጠና በተሰጠው የአውቶቡስ እረዳት እገዛ ይደረግለታል።

ሁሉም የትምህርት ቤት አውቶቡስ ሹፌሮች እና እረዳቶች በሲ/ፒ/አር እና የመጀመሪያ እርዳታ ስልጠና የወሰዱና የብቃት ማረጋገጫ ያላቸው ናቸው። በአደጋ ወቅት፣ ሹፌሮች እና እረዳቶች ተሳፋሪ ተማሪዎችን ደህንነታቸው በተጠበቀ መልኩ እንዲይዙ፣ ሁኔታውን እንዲገመግሙ እና ተገቢ የሆነውን የድጋፍ ሰጭ አካል (ለምሳሌ፥ የስምሪት ዋና ክፍልን እና ወይም የአደጋ ጊዜ አገልግሎት ሰጭዎችን) እንዲያናግሩ ስልጠና ወስደዋል።

ሹፌሮች አውቶብሱን ካለ ችግር አገልግሎት እንዲሰጥ የማድረግ ሃላፊነት አለባቸው። መኪናው በመንገድ ላይ ባለበት ወቅት ለሁሉም ተሳፋሪዎች አስተማማኝ መሆኑን ለማረጋገጥ የቅድመ ጉዞ እና ድህረ ጉዞ ምርመራ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

የአውቶቡስ እረዳቶች ተማሪዎቹን ከሚቀበሉበት አንስቶ እስከ መውረጃቸው ድረስ ተማሪዎቹን ደህንነታቸው በተጠበቀ መልኩ የማጓጓዝ ሃላፊነት አለባቸው። ይህም የሚከተሉትን እና ሌሎችንም ያካትታል - ደህንነት በተጠበቀ መልኩ አውቶብሱ ላይ መውጣት እና መውረድ፣ የልጆች የደህንነት መጠበቂያዎች በጉዞው ወቅት በሙሉ መስራታቸውን ማረጋገጥ፣ እና አውቶብሱ በሚንቀሳቀስበት ወቅት ሁሉም ተማሪዎች የአውቶብሱን ህጎች እየተከተሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ። የአውቶቡስ እረዳቶች በጉዞ ወቅት የሁሉንም ተማሪዎች ሁኔታ ለመከታተል በሚያስችላቸው መቀመጫ ላይ ተቀምጠው የሁሉንም ተማሪዎች ባህሪ ይቆጣጠራሉ። በተጨማሪም፣ ተማሪዎችን ትምህርት ቤት ካደረሱ በኋላ፣ የአውቶቡስ እረዳቶች ሁሉም ተማሪዎች በታቀደው መሰረት መውረዳቸውን እና ምንም አይነት የተማሪዎች የግል ንብረቶች አለመቅረታቸውን ለማረጋገጥ የአውቶብሱን ውስጣዊ ክፍል በሚገባ ይፈትሻሉ።

የአውቶቡስ እረዳቶች እና የአውቶቡስ ሹፌሮች በተማሪው አይ/ኢ/ፒ ላይ በተጠቆመው መሰረት የኢጋዥ መሳሪያዎችን ለመጠቀም እና ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ ስልጠና የተሰጣቸው ናቸው። የምናገለግላቸውን ተማሪዎች ፍላጎት ማሟላት እንችል ዘንድ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ስልጠናዎች የኦ/ኤስ/ኤስ/ኢ ዲ/ኦ/ቲ ሰራተኞች በየዓመቱ የሚወስዷቸው ስልጠናዎች ናቸው።

- አመታዊ የአገልግሎት ግምገማ (AIR-ኤ/አይ/አር) - የተማሪዎችን የአካል ጉዳት አይነቶች እና ባህሪያት፣ የቡድን ተግባቦቶች፣ የእለት ከእለት ሂደቶች (ለምሳሌ፥ የተሽከርካሪ ምርመራዎች ሪፖርቶች፣ የአደጋ ዘገባዎች እና ሰነዶች) ይገመግማል
- እራስን ከአደጋ ተከላክሎ ማሽከርከር
- የዊልቼር ደህንነት
- ሲ.ፒ.አር/የመጀመሪያ እርዳታ
- የሙብት ምላሽ ©
- የዳታ ግላዊነት ስልጠና

## በአውቶቡስ ላይ የተማሪ ባህሪያት

በተጨማሪም የአውቶቡስ ሹፌሩ እና እረዳቱ ቡድን የአውቶቡስ ደህንነትን አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል የተማሪ ምግባርን ሪፖርት የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው። አደገኛ የሆነ የተማሪ ባህሪ ሁኔታ ዘገባ ሲቀርብ፣ ኦ/ኤስ/ኤስ/ኢ ዲ/ኦ/ቲ የተማሪውን ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች፣ የትምህርት ቤት ወይም የአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲን (LEA -ኤል/ኢ/ኤ) ለማነጋገር ይገደዳል። ትምህርት ቤቱ በተማሪው የባህሪ አስተዳደር እና የዲሲፕሊን እርምጃዎች በተመለከተ መመሪያ የመስጠት ሃላፊነት አለበት። በአውቶቡስ ላይ የተማሪዎች ተገቢ ያልሆነ ምግባር የአውቶቡስ አገልግሎቶች መሻርን ሊያስከትል ይችላል።

### በትምህርት ቤት አውቶብሶች ላይ ከተማሪ የሚጠበቁ ባህሪያት

- ተማሪዎች በማንኛውም ጊዜ ሌሎችን ስርአት ባለው መልኩ እና አክብሮት በተሞላበት ሁኔታ ያያሉ።
- ተማሪዎች አውቶቡስ ላይ እያሉ የመዝለል ባህሪ አያሳዩም ወይም ግድየለሽነት በሚታይባቸው ድርጊቶች ውስጥ አይሳተፉም።
- ተማሪዎች ተገቢ ያልሆኑ ቋንቋዎችን አይጠቀሙም።
- ተማሪዎች አውቶቡስ ላይ እያሉ ሞባይል ስልኮችን ወይም ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን እንዲጠቀሙ አይፈቀድላቸውም።
- ተማሪዎች ንብረቶቻቸውን የመጠበቅ ሃላፊነት አለባቸው።
- ተማሪዎች ሁሌም በተገቢው ሁኔታ በወንበር ላይ ሙሉ ለሙሉ መቀመጥ ይጠበቅባቸዋል።
- ተማሪዎች መጽሀፎቻቸውን እና የግል ንብረቶቻቸውን ከአውቶብሱ መተላለፊያ ውጭ ማስቀመጥ ይጠበቅባቸዋል።
- አልኮል እና ትምባሆ መጠቀም ክልክል ነው።
- ተማሪዎች በአውቶቡስ ላይ መብላትና መጠጣት አይፈቀድላቸውም (በአይ/ኢ/ፒ ላይ ካልተመለከተ በቀር)።
- ተማሪዎች ከተፈቀደላቸው ማቆሚያ በፊት ከአውቶቡስ ላይ መውረድ የለባቸውም።
- ተማሪዎች እንዲጠቀሙ የተጠቆመላቸውን እንደ ሄልሜት የመሳሰሉትን አጋዥ መሳሪያዎች በአይ/ኢ/ፒ ላይ በተገለጸው መሰረት ወይም በሚጠበቀው መሰረት አውቶቡስ ላይ ባሉበት ጊዜ ሁሉ ማጥለቅ አለባቸው።
- ተማሪዎች የትምህርት ቤት አውቶቡሱን ማበላሸት፣ ማጥፋት ወይም መጉዳት አይፈቀድላቸውም፣ ወይም የሌሎች ተማሪዎችን ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ መጓጓዝን የሚያስተጓጉል ባህሪ ማሳየት የለባቸውም።

## የወላጅ የመረጃ ማእከል ምንድን ነው?

የወላጅ የመረጃ ማእከል (PRC-ፒ/አር/ሲ) በኦ/ኤስ/ኤስ/ኢ ዲ/ኦ/ቲ፣ በወላጆች፣ በአሳዳጊዎች፣ በትምህርት ቤቶች፣ ማህበራዊ ሰራተኞች፣ ተሟጋቾች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት መካከል እንደዋነኛ የመገናኛ መንገድ በመሆን ያገለግላል። በፒ/አር/ሲ ውስጥ የሚገኙት የደምበኛ አገልግሎት ባለሙያዎች የተማሪዎችን የመጓጓዣ ጉዳዮች በትጋት እና በበቂ ሁኔታ ተደራሽ በማድረግ ጥራት ያለው የደምበኛ አገልግሎት ለመስጠት ተግተው ይሰራሉ።

ወላጆች እና አሳዳጊዎች የሚከተሉትን አይነት ጥያቄዎችን በተመለከተ ፒ/አር/ሲን ማነጋገር አለባቸው፥

- የተማሪዎትን የመጓጓዣ አገልግሎቶች በተመለከተ ጥያቄዎች
- የሚሰጠውን የመጓጓዣ አገልግሎት በተመለከተ ጉዳዮች ወይም ስጋቶች
- ስለ መጓጓዣ አገልግሎት ምስጋና ለማቅረብ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ

ፒ/አር/ሲን በስልክ ቁጥር (202) 576-5000 ከሰኞ እስከ ዓርብ ከጠዋት 5:00 a.m. እስከ ምሽት 7 p.m. ማነጋገር ይችላሉ። በዋና ዋና የመጓጓዣ ሰዓታት ፒ/አር/ሲ ከፍተኛ የሆነ የስልክ ጥሪዎች ያጋጥሙታል (ከ 6-10 a.m. እና ከ 3 -5 p.m.)። በእነዚህ የስልክ ጥሪ በሚበዛባቸው ሰዓታት ላይ የደምበኞች አገልግሎት ባለሙያን ለማነጋገር እባክዎትን በአማካይ ከተለመደው በላይ በመስመር ላይ ሊጠበቁ እንደሚችሉ ልብ ይበሉ። ደዋዮች በሚበዙባቸው በእነዚህ ሰዓታት፣ ምን ማድረግ እንደሚፈልጉ የሚያስመርጥ ሶስት አማራጮች ያለው መልእክት ይቀርብልዎታል፥

1. ቀጥሎ ነጻ የሚሆነው ሰራተኛ መስመር ላይ ገብቶ እስኪያናግርዎት መጠበቅዎን ይቀጥላሉ።
2. የድምጽ መልእክት ትተው የደምበኞች አገልግሎት ተወካይ መልሶ ይደውልልዎታል።
3. ስልኩን ይዘጉታል፣ ወረፋዎት እንደተጠበቀ ይሆናል፣ ከዛም ቀጥሎ ነጻ የሚሆነው የደምበኞች አገልግሎት ተወካይ ይደውልልዎታል።

## አቤቱታ/ቅሬታን ማስመዝገብ

የኦዲት እና ኮምፕሊያንስ ጽ/ቤት ዋና ሚና የቀረቡ ሁሉም ቅሬታዎች/አቤቱታዎች በትክክል ምርመራ የተደረገባቸው እና መፍትሄ ያገኙ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው። ይህ ቢሮ ሁሉም አቤቱታዎች በሰዓቱ ተገቢ ምላሽ የተሰጣቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ጠንክሮ ይሰራል። አቤቱታዎችን በስልክ ቁጥር (202) 576-5000 በመደወል ወይም በኢሜይል osse.dot@dc.gov ማቅረብ ይቻላል።

## አቤቱታ/ቅሬታ ካቀረቡ በኋላ የሚከተለው ምንድን ነው?

1. የፒ/አር/ሲ የደምበኞች አገልግሎት ባለሙያ አቤቱታዎችን ተቀብሎ ለአቤቱታ አቅራቢው አቤቱታዎችን የሚከታተል ባላሙያ ከ3-5 ባሉት የስራ ቀናት ውስጥ ጉዳዩን እንደሚከታተል ይገልጻል፤ በባህሪያቸው ከደህንነት ጋር የሚያያዙ ቅሬታዎች በ 24 ሰዓት ውስጥ ወይም በሚቀጥለው የሥራ ቀን ምላሽ ይሰጣቸዋል
2. የቀረበውን ቅሬታ የሚከታተል የቅሬታ ባላሙያ ይመደባል
3. የቅሬታ መርማሪ ባለሙያው ቅሬታ አቅራቢውን ያነጋግራል

**እባክዎትን ልብ ይበሉ፥** የቅሬታ መርማሪ ባለሙያውን ለማነጋገር ቀጥተኛ የሆነ የስልክ መስመር የለም። ያቀረቡት አቤቱታ ያለበትን ደረጃ ለመከታተል ከፈለጉ፣ ፒ/አር/ሲን በስልክ ቁጥር (202) 576-5000 ማነጋገር አለብዎት።

# ተደጋግመው የሚነሱ ጥያቄዎች

### 1. የልጄ አውቶቡስ የት ነው ያለው? በሳምንቱ ውስጥ አውቶብሱ በተለያየ ጊዜ የሚደርሰው ለምንድን ነው?

የመንገድ መዘጋጋት እና የአየር ሁኔታ ለውጥ ኖሮ በመስመሩ ላይ ትንሽ ለውጥ ካስከተለ፣ አውቶብሱ በየቀኑ እርሶ ቤት ጋር በተመሳሳይ ጊዜ አይደርስም ማለት ነው። ለምሳሌ፥ የእርሶ ልጅ ከመሳፈሩ በፊት የሚሳፈሩ ተማሪዎች በህመም ምክንያት ትምህርት ቤት የማይሄዱ ከሆነ፣ አውቶብሱ እርሶ ቤት ጋር ቀድሞ ይደርሳል ማለት ነው፤ በሌላ በኩል አውቶብሱ በሚያልፍበት መንገድ ላይ የግንባታ ስራ እየተካሄደ ከሆነ፣ አውቶብሱ ዘግይቶ ይደርሳል ማለት ነው። አውቶብሱ የደረሰበትን ቦታ ለማወቅ ከፈለጉ እና መቼ እንደሚደርስ ለማወቅ ከፈለጉ፣ የወላጅ የመረጃ ማእከልን ደውለው ያነጋግሩ።

### 2. የልጄ መስመር ሊቀየር ይችላል? ሌላ ሹፌር ወይም እረዳት እንዲቀየር መጠየቅ እችላለሁ?

መስመሮቻችን እንዴት መሆን እንዳለባቸው ለመወሰን እና በዛ መስመር ማን እንደሚሰራ ለመወሰን ወራትን የፈጀ እቅድ እናወጣለን። በአንድ መስመር ላይ የሚጠቀሙ በርካታ ተማሪዎች በመኖራቸው፣ መስመሩ እና ሰራተኞቹ ቋሚ መሆን አለባቸው። ነገር ግን፣ በጣም መሰረታዊ የሆኑ አሳሳቢ ነገሮች ካሉ፣ አማራጮችን ለመወያየት ወደ ወላጅ መረጃ ማእከል ይደውሉ።

### 3. ልጄ አውቶብሱን መጠበቅ ያለበት መቼ እና የት ነው? እረዳቱ በሩን ማንኳኳት አለበት? አውቶብሱ ቆሞ ምን ያህል ጊዜ ልጄን ይጠብቀዋል?

ተማሪዎች እና ወላጆች ለ30- ደቂቃው የመጠበቂያ ክፍተት በሙሉ ዝግጁ ሆነው መጠበቅ እና በመስኮት በኩል ወይም የፊት ለፊት በር በኩል የአውትብሱን መድረስ መከታተል አለባቸው። አውቶብሱ እርሶ ቤት ጋር ከደረሰ በኋላ፣ መራመድ ለሚችሉ ልጆች ሶስት ደቂቃ፣ ዊልቼር ለሚጠቀሙ ልጆች ደግሞ አምስት ደቂቃ ያህል ይጠብቃል። የአውቶቡስ እረዳቱ በር ማንኳኳት አይጠበቅበትም። በመስመሩ ላይ ያሉትን ሁሉንም ተማሪዎች በተመደበው የመጫኛ ሰዓታቸው ለመቀበል እና ትምህርት ቤት በሰዓቱ ለመድረስ ይቻል ዘንድ፣ አውቶብሱ ጥብቅ የሆነ የጉዞ መርሃግብር መከተል አለበት።

### 4. ከትምህርት ቤት አውቶቡስ ሌላ አማራጮች አሉ?

እራሳቸውን ችለው ሜትሮ መጠቀም የሚችሉ ልጆች ወደ ትምህርት ቤት ለመጓዝ የዲሲ ዋን ካርድ ለመቀበል ብቁ ናቸው። በተጨማሪም፣ ብቁ የሆኑ ልጆቻቸውን እራሳቸው ከቤት ወደ ትምህርት ቤት ማመላለስን ለሚመርጡ ወላጆች ተመላሽ ገንዘብ ይኖራቸዋል። እባክዎትን እርዳታ ለማግኘት የልጅዎትን ትምህርት ቤት ወይም ፒ/አር/ሲን ያነጋግሩ።

### 5. ልጄ ቢታመም የማሳውቀው ለማን ነው?

ለፒ/አር/ሲ በስልክ ቁጥር (202) 576-5000 በመደወል ወይም osse.dot@dc.gov በሚለው የኢሜይል አድራሻ ኢሜይል በመላክ ልጅዎት መታመሙን በመግለጽ ትምህርት ቤት የማይመጣ መሆኑን ያሳውቁን፤ ይህም አውቶብሱ እርሶ ቤት ድረስ እንዳይመጣ ያግዛል። እባክዎትን ስምዎትን፣ የልጅዎትን ስም፣ እና የትምህርት ቤቱን እና የአውቶብሱን የመስመር ቁጥር መግለጽዎን ልብ ይበሉ (የሚኖር ከሆነ)።

## 6. ከሰዓት በኋላ ልጄ ከትምህርት ቤት ሲመለስ እኔ በቤት ውስጥ ከሌለሁስ?

አስቸኳይ ነገር ባጋጠመ ወቅት ወደ ፒ/አር/ሲ በመደወል በአድራሻዎት ሌላ ሰው ልጅዎትን እንዲቀበል መፍቀድ ይችላሉ። ይህ ግለሰብ እድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ እና ለአውቶቡስ እረዳቱ ትክክለኛ የሆነ መታወቂያ ማሳየት የሚችል መሆን አለበት። ልጅዎትን የሚቀበል በቦታው ማንም ከሌለ፣ ፒ/አር/ሲ እርስዎን ደውሎ ለማነጋገር የሚሞክር እና ሁለተኛ ልጁን የማውረድ ሙከራ የሚደረግ ይሆናል። ከእነዚህ ሙከራዎች በኋላ ልጅዎት የማይወርድ ሲሆን ወደ ዲሲ የልጆች እና የቤተሰብ አገልግሎቶች ኤጀንሲ (CFSA-ሲ/ኤፍ/ኤስ/ኤ) የሚወሰድ ይሆናል።

## 7. የመገኛ አድራሻዬን ወቅታዊ የማደርገው እንዴት ነው? በትምህርት ዓመቱ ወቅት ቤት ወይም ትምህርት ቤት ብንቀይር ምን ይከተላል?

ማንኛውም አይነት የመገኛ አድራሻ ላውጥ (ለምሳሌ፥ አድራሻ፣ ስልክ ቁጥሮች) ከኖረ፣ የልጅዎትን ትምህርት ቤት ያነጋግሩ። ኦ/ኤስ/ኤስ/ኢ ዲ/ኦ/ቲ የስልክ ቁጥሮች እና አድራሻዎች የመሳሰሉትን መረጃዎች መቀየር አይችልም። ቤት ለመቀየር የሚያስቡ ከሆነ፣ አዲስ የማጓጓዣ መጠየቂያ ቅጽ (TRF-ቲ/አር/ኤፍ) ለማስገባት እንዲቻል ለማድረግ እባክዎትን የልጅዎትን ትምህርት ቤት ቀደም ብለው ያነጋግሩ። ከአዲሱ አድራሻ ወደ ትምህርት ቤት ወይም ከትምህርት ቤት ወደ አዲሱ አድራሻ የማጓጓዝ አገልግሎት ለመጀመር አዲስ ቲ/አር/ኤፍ ያስፈልጋል።

## 8. የአውቶቡስ ሹፌር ወይም እረዳት ለልጄ የሚሆን መድኃኒት ትምህርት ቤት ሊያደርሱልኝ ይችላሉ? የአውቶቡስ ሹፌር ወይም እረዳት በአውቶብሱ ውስጥ መድኃኒት ሊሰጡ ይችላሉ?

ፍቃድ ባለው ነርስ ካልሆነ በቀር መድኃኒት በአውቶቡስ ውስጥ ሊጓጓዝ ወይም ሊሰጥ አይችልም። ልጅዎት በጉዞ ወቅት ለመድኃኒት እርዳታ ፍቃድ ያለው ነርስ የሚፈልግ ከሆነ፣ ይሄ ጉዳይ በአይ/ኢ/ፒ ቡድኑ መጠየቅ አለበት።

# ተጨማሪ የመረጃ እና የመገኛ ዝርዝሮች

ከአይ/ኢ/ፒ ጋር፣ ከአድራሻ ጋር እና ከስልክ ቁጥር ለውጥ ጋር፣ እና ከድጋፍ መስጫዎች ለውጦች ጋር የተገናኙ ነገሮችን በተመለከተ ላሉዎት ጥያቄዎች እባክዎትን የልጅዎትን ትምህርት ቤት ያነጋግሩ።

| **የመረጃው መገኛ** | **ስልክ ቁጥር** | **ማነጋገር ያለብዎት መቼ ነው** |
|---|---|---|
| ኦ/ኤስ/ኤስ/ኢ ዲ/ኦ/ቲ የወላጅ መረጃ ማእከል (ፒ/አር/ሲ) | (202) 567-5600 | የአውቶቡስ መድረሻ ሰዓትን እና መርሃግብርን በተመለከተ ለሚነሱ ጥያቄዎች፤ ቅሬታ ለማቅረብ፤ መጥፎ የአየር ሁኔታ መረጃን በተመለከተ |
| የእስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ጽ/ቤት (OSSE-ኦ/ኤስ/ኤስ/ኢ) | (202) 727-6436 | ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ስለሚሰጡ አገልግሎቶች አጠቃላይ ጥያቄዎች |
| የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች የግለሰባዊ ትምህርት | (202) 442-4800 | የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለሚከታተሉ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ወላጆች መረጃ |
| የዲሲ የልጆች እና የወላጅ አገልግሎቶች ኤጀንሲ (CFSA-ሲ/ኤፍ/ኤስ/ኤ) | (202) 442-6100 | |
| ሲ/ኤፍ/ኤስ/ኤ ሆትላይን | (202) 671-SAFE | በልጆች ላይ የሚደረግ በደል ውንጀላዎችን ሪፖርት ለማድረግ |
| የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የመንግስት አገልግሎት ጥያቄ | 311 | ስለዲሲ መንግስት አገልግሎቶች፣ ቁጥሮች እና ... ጥያቄዎች በተመለከተ ሁሉን በአንድ ያጣመረ የጥሪ ማእከል |